የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ – ግንቦት ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11[th] Year No. 31
Addis Ababa 24[th] May, 2005

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፯/፲፱፻፺፯ ዓ·ም
"የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል አከባበር ብሔራዊ ምክር ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.......... ገጽ ፫ሺ፺፰

## CONTENTS

Council of Ministers Regulation No. 117/2005 "Ethiopian Millennium Festival National Council Establishment Council of Ministers Regulations ........................................... Page 3098

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፯/፲፱፻፺፯ የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል አከባበር ብሔራዊ ምክር ቤት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል አከባበር ብሔራዊ ምክር ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፯/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ "የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል" ማለት ኢትዮጵያ በምትከተለው የዘመን አቆጣጠር መሠረት ሦስተኛው ሚሌኒየም ከመግባቱ ቢያንስ ከሦስት ወር በፊት ጀምሮ ዓመቱን በሙሉ ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ነው ።

፫· <u>መቋቋም</u>

፩· የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል አከባበር ብሔራዊ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ።

፪· የምክር ቤቱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል ።

### *Council of Ministers Regulations No. 117/2005*
### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO ESTABLISH THE ETHIOPIAN MILLENNIUM FESTIVAL NATIONAL COUNCIL*

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995.

1. *Short Title*

   This Regulation may be cited as the "Ethiopian Millennium Festival National Council Establishment Council of Ministers Regulation No. 117/2005."

2. *Definition*

   In this Regulation "the Ethiopian Millennium Festival" means a period of one year starting from at least three months prior to the beginning of the third millennium in accordance with the Ethiopian calendar.

3. *Establishment*

   1) The Ethiopian Millennium Festival National Council (hereinafter the "Council") is hereby established.
   2) The Council shall be accountable to the Prime Minister.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፬· የምክር ቤቱ ዓላማዎች

ምክር ቤቱ የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል አከባበር አጋጣሚን በመጠቀም የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል ፣

፩· መላው ኅብረተሰብ በልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ረገድ የጋራ የሆነ አገራዊ አመለካከት በመገንባት የተሻለ ገጽታ ያላት ኢትዮጵያን ለማየት ብሩህ ተስፋ ሰንቆ ወደ አዲሱ የኢትዮጵያ ሚሌኒየም እንዲሸጋገር የማስቻል ፣

፪· ኅብረተሰቡን በልማትና በመልካም አስተዳደር ሀገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ በማንቀሳቀስ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር የማስቻል ፣

፫· በመንግሥትና በሕዝቦች ሙሉ ተሳትፎ የአገሪቱን መልካም ገጽታ ሊገነቡ የሚችሉ ብሔራዊ እሴቶቻችን ለመላው ዓለም በማስተዋወቅ አገሪቱን በኢንቨስትመንት ፣ በቱሪዝም ፣ በንግድና በሌሎች መስኮች ተመራጭነት የሚያሰጣት መልካም ገጽታ እንዲገነባ የማስቻል፣

፬· ለመላው ኅብረተሰብ ፣ ለወጣቱ ትውድና በአጠቃላይ ለመላው ዓለም ብሔራዊ ዓላማዎቻችንን ፣ ተልዕኮአችንንና የትኩረት አቅጣጫዎቻችንን የሚያመላክቱ ዐበይት መልዕክቶችን ለማስተላለፍ የማስቻል ።

፭· የምክር ቤቱ አባላት

ምክር ቤቱ ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡ አባላት ይኖሩታል ፣

፩· ከፌዴራልና ከክልል መንግሥታት ፣
፪· መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ፣
፫· ከግል ባለሃብቶች ፣ ከታዋቂ ግለሰቦች ፣ ከኪነጥበብ ባለሙያዎች ፣ በውጭ አገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ፣ እና
፬· ለበዓሉ አከባበር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ከሚችሉ ሌሎች አካላት ።

፮· የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፣

፩· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማስፈጸም የሚረዱ መርሀ ግብሮችንና ፕሮጀክቶችን ለመንደፍ የሚያስችል ሃሳብ ያቀርባል ፣ መንግሥትን ያማክራል ፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል ፣

፪· ለሚሌኒየም በዓሉ አከባበር በሚደረገው ዝግጅት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋሞችና ድርጅቶች ፣ በአጠቃላይ መላው ኅብረተሰብ ፣ እንዲሁም በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያበረታታል ፣

፫· ለበዓሉ አከባበር የሚያስፈልገውን የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በማፈላለግ ያሰባስባል ፣

፬· ዓላማውን ከግብ ለማድረግ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል ።

፯· የምክር ቤት አካላት

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል ፣

፩· በክልል ፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ የሚቋቋሙ ምክር ቤቶች ፣
፪· እንዳስፈላጊነቱ በውጭ አገር የሚቋቋሙ ምክር ቤቶች ፣
፫· የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ፣ እና
፬· ብሔራዊ ጽሕፈት ቤት ።

፰· ስለምክር ቤቱ ፕሬዚዳንትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት

የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በመንግሥት ይመደባሉ ።

4. *Objectives of the Council*

The Council shall, in conjunction with the event of the Ethiopian Millennium Festival, have the following objectives:

1) to enable the whole society to have shared vision with respect to national issues on development and building democratic system and thereby enter the new Ethiopian Millennium with the hope of seeing a better Ethiopia;
2) to mobilize the society around national development and good governance issues and thereby create national consensus;
3) to promote, through the concerted efforts of the Government and all citizens, the national heritages of the country through out the rest of the world with a view to image building in investment, tourism, trade and other aspects of the country;
4) to convey the country's major national objectives, missions and strategic interests to the society, the youth and the world in general.

5. *Members of the Council*

Members of the Council shall be drawn from the following organs:

1) the Federal and Regional States;
2) governmental and non-governmental institutions;
3) private investors, renowned individuals, artists, the Ethiopian diasporas and friends of Ethiopia; and
4) other organs that could play a role in the event.

6. Powers and Duties of the Council

The Council shall have the powers and duties to:

1) forward proposals and advice the Government on the formulation of programmes and projects designed for the realization of the objectives stated under Article 4 of this Regulation;
2) encourage the active participation of governmental and non-governmental institutions and enterprises, the society in general, as well as Ethiopian living abroad and persons of Ethiopian origin in the preparatory activities of the Millennium Festival;
3) mobilize the material and financial support required for the Festival from domestic and foreign sources;
4) perform such other activities as may be necessary for the realization of its objectives.

7. *Organs of the Council*

The Council shall have the folowing organs:

1) Councils to be established at regional, zonal and wereda levels;
2) Councils to be established abroad as may be necessary;
3) an Executive Committee; and
4) a National Secretariat.

8. *The President and Members of the Executive Committee of the Council*

The President of the Council and members of the Executive Committee shall be assigned by the Government.

፱· የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር

የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ፤

፩· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ መሠረት ለምክር ቤቱ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ባግባቡ መፈጸማቸውን በበላይነት ይቆጣጠራል ፤

፪· የምክር ቤቱንና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ስብሰባዎች ይመራል ፤

፫· የምክር ቤቱን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ጽሕፈት ቤት የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይቆጣጠራል ፤ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል ፤

፬· ለኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል አከባበር የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል ።

፲· የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

የምክር ቤቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ፤

፩· የምክር ቤቱን አስተያየት መሠረት በማድረግ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማስፈጸም የሚረዱ መርሀ ግብሮችን ፤ ፕሮጀክቶችንና የአፈጻጸም ዕቅዶችን በመንደፍ ለመንግሥት ያቀርባል ፤ ሲፈቀድም ተከታትሎ ያስፈጽማል ፤

፪· የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል አከባበር ሲጠናቀቅ በሥሩ በመከናወን ላይ ያሉትን መርሀግብሮችና ፕሮጀክቶችን ለመንግሥት አቅርቦ በማስወሰን አግባብነት ላላቸው መንግሥታዊ አካላት ያስረክባል ፤

፫· ለኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል አከባበር የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል ።

፲፩· ስለምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት

፩· የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ፤

ሀ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ይኖረዋል ፤

ለ) ዋና መሥሪያ ቤቱ በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ከአገር ውጭ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል ፤

ሐ) በመንግሥት በሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱና ምደባቸው በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚጸድቅ ረዳት ዳይሬክተሮች ይኖሩታል ፤

መ) ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት የሚውጣጡና ሌሎች ጊዜያዊ ሠራተኞች ይኖሩታል ።

፪· ጽሕፈት ቤቱ የምክር ቤቱን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ይከታተላል ፤ ይፈጽማል።

፲፪· የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

፩· ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ያወጣል ።

፪· የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የራሱን የስብሰባ ሥርዓትና የምክር ቤቱን መተዳደሪያ መመሪያ ያወጣል ።

፲፫· በጀት

፩· የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የሥራ ማስኬጃ በጀት በመንግሥት ይመደባል ።

፪· ለኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል አከባበር ዝግጅት የሚያስፈልገው ወጪ ፤

ሀ) በመንግሥት በሚመደብ በጀት ፤

ለ) በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ከሚደረጉ ኤግዚቢሽኖች ፤ ባዛሮችና ሌሎች የገቢ ማሰባሰቢያ መድረኮች በሚገኝ ገቢ ፤

ሐ) ከልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችና ተቋሞች በሚገኝ ድጋፍ ፤ እና

መ) ከሌሎች ምንጮች በሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ ፤

የሚሸፈን ይሆናል ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚገኝ ገንዘብ በምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ስም በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ ሆኖ ለኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል ዝግጅት ማስፈጸሚያ ይውላል።

9. *Powers and Duties of the President*

The President of the Council shall:

1) supervise the proper execution of the powers and duties of the Council under Article 6 of this Regulations;
2) preside over the meetings of the Council and the Executive Committee;
3) supervise and follow up the activities of the Executive Committee and the Secretariate of the Council;
4) perform such other activities as may be necessary for the celebaration of the Ethiopian Millennium Festival.

10. *Powers and Duties of the Executive Committee*

The Executive Committee of the Council shall:

1) formulate and submit to the Government, based on the opinions of the Council, programs, projects and action plans designed for the realization of the objectives state under Articles 4 of the this Regulation and, upon their approval, implement same;
2) at the end of the Ethiopian Millennium Festival, hand over on-going programs and projects to the appropriate government organs on the basis of decisions by the Government;
3) perform such other activities as may be necessary for the celebration of the Ethiopian Millennium Festival.

11. *Secretariat of the Council*

1) The Secretariate of the Council:
   (a) shall have it sown juridical personality;
   (b) shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices abroad, where necessary;
   (c) shall be headed by a Director General to be assigned by the government and, where necessary, Assistant Directors whose assignment shall be approved by the Executive Committee;
   (d) shall have personnel to be assigned on the basis of socondment from different governmental and non-governmental insitutions and other contractual employees.
2) The Secretariat shall be responsible for the day-to day operations of the activities of the council.

12. *Rules of Procedures*

1) The Council shall adopt its own rules of procedure for conducting meetings and the passing of decisions.
2) The Executive Committee shall adopt its own rules of procedures and the operational manual of the council.

13. *Budget*

1) The recurrent budget of the Secretariate of the Council shall be approprated by the government.
2) The expenses to be incurred in connection with the celebration of the Ethiopian Millennium Festival shall be covered by:
   (a) budgetary appropriations by the Government;
   (b) funds generated through exhibitions, bazaars and other fund mobilization events to be conducted locally or abroad;
   (c) contributions by the different sectors of the society and institutions;
   (d) financial support from other sources.
3) The fund to be mobilized pursuant to sub-article (2) of this Article shall be deposited in a bank account to be opened in the name of the Secretariat of the Council and shall be expended to give effect to the celebration of the Ethiopian Millennium Fesival.

፲፬. <u>ስለሂሳብ መዛግብት</u>

፩. የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል ።

፪. የጽሕፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌዴራሉ ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ ።

፲፭. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

የምክር ቤቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል ።

፲፮. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከግንቦት ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

14. *Books of Accounts*

1) The Secretariat of the Council shall keep complete and accurate books of accounts.
2) The books of accounts and financial documents of the Secretariat shall be audited by the Federal Auditor General or by auditors assigned by him.

15. *Power to Issue Directives*

The Executive Committee of the Council may issue directives necessary for the implementation of this Regulations.

16. *Effective Date*

This Regulaltions shall come into force on the date of 24th day & May 2005.

Done at Addis Ababa, this 24th day of May, 2005

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት